የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የረመዿን የመጨረሻዎቹ አስሩ ቀናት የገቡ ጊዜ ሌሊቱን ህያው ሆነው ያሳልፋሉ፤ ቤተሰባቸውንም ያነቃሉ፤ ይበረቱና ሽርጣቸውንም ያጠብቁ ነበር።

ከአማኞች እናት ከዓኢሻ - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የረመዿን የመጨረሻዎቹ አስሩ ቀናት የገቡ ጊዜ ሌሊቱን ህያው ሆነው ያሳልፋሉ፤ ቤተሰባቸውንም
ያነቃሉ፤ ይበረቱና ሽርጣቸውንም ያጠብቁ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የረመዿን የመጨረሻዎቹ አስሩ ቀናት የገቡ ጊዜ ምሽቱን ሁሉ በተለያዩ አምልኮዎች ህያው ሆነው ያሳልፉ ነበር። ቤተሰባቸውንም ለሶላት ይቀሰቅሱ ነበር። ከልማዳቸው ተጨማሪ በሆነ መልኩ በአምልኮ ይታገሉ ነበር። ከሚስቶቻቸው ጋር መተኛትንም ትተው በአምልኮ ብቻም ያሳልፉ ነበር።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/4944